# <u>እንዳዲስ እንጀምር?</u>
# <u>ያዲስ ፕሮጀክት ጥንስስ ሓሳብ</u>

*መስከረም* 12, 2000 *ዓ.ም*

*አገራችን የብዙ ዘመን ታሪክ እንዳላት የታሪክ አዋቂዎች ይነግሩናል። በዚህ በረዢም ጉዟችን ህዝባችን በጎዉንም ክፉዉንም አይቷል። የምንኮራበት ታሪክ እንዳለን ሁሉ አንገታችንን የሚያስደፉም አልጠፉም። ብዙዎቻችን የምናውቀው ስለሆነ ስላለፈው ታሪካችን ደጋገሞ ማውሳቱ ትንሽ ያሰለች ይሆናልና አልደጋግመውም።*

*ብዙ ስናወራ በዙ ወርቃማ ጊዜያችንን አቃጠልን። የህዝባችን ችግር ግን እስካሁን ድረስ በነገር አላቃለልነውም - አሁንም እንዳለ ነው።ወግና ወሬ ጎድተዉን እንደሆን እንጂ አልረዱንም። አሁን አቅጣጫችንን መርምረን አካሄዳችንን የምናስተካክልበት ጊዜ ደርሷል። ጊዜው የተግባር ነው። አሮጌ ዘመን አልፎ አዲሱ ሲተካ መጪው ዘመን የደስታ፣ የጥጋብና የሠላም እንዲሆን መመኘት የቆየ ባህላችን ነው። በዚህ በሺህኛው ዘመን ደግሞ ተግባር ታክሎበት ምኞቱን እውን እናደርገው ዘንድ ባነድነት እንድንነሳ ያስፈልጋል።*

*ታድያ ዓላማችን ሠላምና ዕድገት ከሆነ ያለን ምርጫ አነድ ነው ብየ አስባለሁ። ወደፊት መራመድ አለብን። የህዘባችንን የበሽታ ጥቃት፣ ሰቆቃና ረሃብ መወገድ ይኖርበታል ብለን ካመንን ወደፊት ከመራመድ ሌላ - ሌላ አማራጭ የለንም።*

*አንድ ምንም የማያከራክረን ወሳኝ ቁም-ነገር አለ። ይኸወም ሁሉም ኢትዮጵያዊ ያላንዳች ጥርጣሬ ከ ኢትዮጵያ ምድር ጠኔና ረሃብ መወገድ እንዳለበት ከልብ መፈለጉንና ይህንን ፍላጎት እውን ለማድረግ እያንዳንዱ በግልም ሆነ በቡድን እንቅስቃሴ ማድረጉን ነው። የሚያጠራጥረን ነገር ግን እነዚህ እንቅስቃሴዎች አዋነታዊ እንድምታ አስከትለዋል ወይ የሚለው ጥያቄ ነው። ያለፈው አካሄዳችን እንደምስክርነት ከተወሰደ ያለፉት ዓሥርት ዓመታት እንቅስቃሴዎቻችን አሉታዊነታቸው ያደላል የሚል ግምት አለኝ።*

*ይህ አዲስ የያዝነው የ ኢትዮጵያ ምዕተ-ዓመትና የሶስተኛው ሺሕ ዘመን መግቢያ አዲስ አስተያየት፣ አዲስ መንፈስና አዲስ ራዕይ እንዲኖረን ይጋብዘናል። በዚህ መንፈስ በመነሳሳት ነው አንባቢዎቼን ለመሞገት (ቻለንጅ -ለማድረግ) ባጭሩ የምሞክረው።*

*ብዙ ጊዜ ከባድም ይሁኑ በጣም ቀላል የሆኑ ችግሮችን መፍታት የሚቻለው ቀላል የሆኑ መፍትሂዎችን (ወይም የመፈትሂ ሃሳቦችን) በማቅረብ ነው። ለምሳሌ የወንዝ ዉሃ ወይም የዝናብ እጥረት ባለበት አካባቢ የጉድጓድ ዉሃ በማውጣት ድርቅንና ከድርቅ ጋር ተያይዞ የሚመጣ ረሃብን መከላከል ይቻላል። የገጠሬውን ኑሮ በመጠኑም ማቃለል ዪቻላል።*

ትላልቅ ነገሮች በትናንሽ ሁኔታዎችና ግንዛቤዎች ነው የሚጀመሩት።

ባልሳሳት፣ የመጀመርያው ዓለም ጦርነት የተጀመረው አንድ ሰው በትንሽ ምክንያት ስለተገደለ ነው። ኤሌክትሪክ የተፈጠረው ሚስተር ማይክል ፋራዳይ ኤሌክትሪክ መፍጠር አለብኝ ብለው ሰለተነሱ አይደለም። ጥቃቅን ግንዛቤዎች ተደማምረው መንገዱን እንዲያዩ ስለረዷቸው እንጂ። ሌሎች ብዙ ነገሮችም እንደዚሁ።

ከሩቁ ሳንሄድ በአገራችን ሰሞኑን የሚሰማው አዎንታዊ ወሬ የብሩህ ሚለኒየም ተስፋ ውጤት ነው። ቴዲ አፍሮ የርቅ መልክተኛ ሆኖ ጂማ ውስጥ በመገኘት በህዝቡ መካከል የነበረውን የሻከረ ግንኙነት ባንድ ሌሊት ወደ ፍቅርና መቻቻል ለመቀየር ምክንያት እንደሆነው፣ በጋምቤላ ውስጥ በተለያዩ ብሄረሰቦች መካከል የሚታየው የሚለኒየሙ አዲስ መንፈስ፣ ባዲስ አበባና ሌሎች የ ኢትዮጵያ ከተሞች የሚስተዋለው ያዲሰ ተስፋ መንፈስ በጅምላው የታላቅ ምርምርና ፕላን ውጤት ሳይሆን የህዝቡ የተስፋ ጭላንጭል ማየት - የብሩህ ዘመን ተስፋ ውጤቶች ይመስሉኛል።

እኛ  የኢትዮጵያ ምሁራን ግን ለፖለቲካው ችግርም፣ ለ ኤኮኖሚ ቀውሱም፣ ለማህበራዊ ችግሩም ሁሉ የምናቀርበው መፍትሄ ሁሉም ጊዜ ፖለቲካዊ ነው። ያለፉት አርባ-ሰላሳ ዓመታት አካሄዳችን ይህንን ነው የሚመሰክረው። ሁሉንም ችግር በየዘርፉ ከመቅረፍ ይልቅ ሁሉንም ሃይላችንን አንድ ነገር ላይ ማዋልን እንመርጣለን። የተለያየ የፖለቲካ እምነት ያላቸው ጎራቸውን ለይተው ጦር ሲማዘዙ ሕዝቡ ተረስቶ በሽታና ረሃብ አንዴም ባንድነት ሲል ደግሞ በፈረቃ እየተሳለቁበት ጊዜ አልፎ ሌላ ጊዜ ይተካል። እኛ ምሁራንም ሆንን የምሁራን ተከታዮች ጎረኞቹን አይዟችሁ በማለት ጠቡ እንዲካረር ከማድረግ ይልቅ እንደ አንድ አካል የሚጠበቅብንን የማረጋጋትና ያርቆ አስተዋይነት ሥራ ስናከናዉን አንታይም።

ፈረንጆች እንደሚሉት ሁሉንም እንቁላላችንን ባንድ ቅርጫት አናስቀምጣለን። ዕድል ሳይቀና ቀርቶ ቅርጫቱ ከተንገራገጨ ኪሳራ ውስጥ አንገባለን። እናም ዝናብ በሌለብት ቦታ ውሃን ከጉድጋድ ማውጣት እያለ (አጭር መንገድ) የሌለ የዝናብ ውሃ እንዴት አድርገን እነደምናወርድ ስንነታረክ ጊዜው ያለፋል። ደመናውን ባርቲፊሽያል መንገድ ፈጥረን፤ የ ኤሌክትሪክ ከረንት/ጨረር ልከን ዝናበ ማምጣት ይቻላል የሚል አይነት ክርክር ውስጥ ራሳችንን እናጠልቃለን። ያን ያክል ሃይልና ዕዉቀት ቢኖረን ኖሩ ከነገረ ቀደሙ ስለዉሃና ከዚያም ጋር ተያይዞ ስለሚመጣው የመራብ ችግር አናወራም ነበር።ይህ አካሄዳችን እንዳከሰረን ነው እኔ የምገነዘበው።

እኔ የምለውና የሚመስለኝ አዲስ እይታ በመንፈሳችን እንዲሰርጽ ነው። ፖለቲካ መሪዎቹ ፖለቲካውን ይከታተሉ። አኛም የሚመስለንን ፖለቲካ መስመር እንደግፍ/እንከተል።ግን ምንም ይሁን ምን ፖለቲካችን ላገራችን፣ ለህዝባችን የጉሰቁልና ኑሮ ለማስወገድ የምናደርገውን እንቅስቃሴ  ሊያስተጓጉልብን ግን ፈጽሞ መፍቀድ የለብንም።

ሌላ ብዙ ምሳሌዎችን ማነሳት ይቻላል። ግን ውሃ እጥረትን በሚመለከት፡-

በውጭ አገር ተሰበጣጥረን የምንኖር ኢትዮጵያውያን ሁሉ -ከቁጥራችን አነፃር ዒምንት በሆነ ገንዘብ መጠን እንኳን ብንጀምር - በ ዓመት አንድ ሚልዮን የ አሜሪካን ዶላር ብናዋጣ አንድ መቶ ሽሕ (100 000) የውሃ ጉድጋድ መቆፈር እንችላለን። እያንዳንዱ የዉሃ ጉድጓድ አስር ቤተሰቦችን እንኳን ነጻ ቢያወጣ በዓመት ከ አንድ ሚልዮን ቤተሰቦች በራሳቸው የሚተማመኑና ራሳቸውን የሚችሉ ኢትዮጵያውያንን አተረፍን ማለት ነው።

ታድያ፣ ይህንን የመሰለ ጀግንነትና ጀብዱ አይደለም'ንዴ ህዝባችን የሚፈልገው? ምን ነክቶን ነው - ይህን የመሰል ሃይል እያለን - ህዘባችን ሲቸገርና ሲጠማ የምንበግነውና የምንታመመው? ካላጣነው ገንዝብ? እንዲያው ስናስበው በሳምንት አንዲት ቀን እንኳን አንዲት ሲኒ ቡና በመተው - አንድ ቡና መግዣ ብር ብናስቀምጥ ባነድ አመት ውስጥ 52 ብር ትሆንና እንዳው በትንሹ 100 000 ስደተኞች (ዲያስፖራዎች) ከ አመስት ሚልዮን ብር በላይ አዋጣን ማለት እኮ ነው! ከጉድጓድ ዉሃ አልፎ የጤና ጣቢያዎችና ሌላም ሌላም ነገር ማድረግ ይቻላል። የበላ የተደላደለ ህዝብ የመማር ዕድል ያገኛል፣ ስለመብቱ ይታገላል፡ ፍትሃዊ አስተዳደርን ይሻል፣ አዲሰ ባገኘው ቁሳዊና ባህሪያዊ እድገት ተጠቅሞም የሚሻውን ያደርጋል/ያገኛል።

እኔ ይችን ለማለት ብቻ ነው የፈለግኩት። እጅግ ታላቅ ሓይል ነን እኛ ዲየስፖራዎች። ያገራችንን ዕድገት ለማፋጠን፡ በዕደሜያችን ረሃብን በርግጠኝነት ለማጥፋትና በሽታን ባብዛኛው ለማስወገድ ወሳኝ አስተዋጽኦ ማድረግ እንችላለን። የሚያስፈልገን ነገር ቢኖር አዲስ አስተሳሰብና አዲስ ዝግጅት ነው።

እሰካሁን ድረስ በቆየና ዶግማቲክ (ግትረኛ) አስተሳሰብ ተተብትበን ፖለቲካዊ ፍትህ ከሌለ የኤኮኖሚ እድገት አይኖርም እያልን ለሌላ አስተሳሰብ ጆራችንን አንሰጠም ነበር። የህዝባችንን ብሶት ቅንጣት ያህልም ሳናሻሽል አብረን ስንበግን ከርመናል። ከንግዲህ ነገሮችን አስፍተን ማየት ያለብን ይመስለኛል።

ይኸው እያየነው ነው። ሁላችንንም የሚያስደስት መንግስት ሳይኖር እድገት ባገራችን እየታየ ነው። ስለዚህም የኢትዮጵን ህዝብ የመገናኘት እድሉ አለ። የሚመጣውን ተፅእኖ ሁሉ ተቋቁመን የምንሰራበት ምቹ ሁኔታ አለ። ውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ በፖለቲካ እይታው ሊለያይ ዪችላል። የህዝቡን የ ኤኮኖሚ ችግር ለማሰወገድ ያለው ፈላጎት ግን አንድ ነው። ይህ የጋራ አላማ ሁላችንንም ስለሚያስተሳስረን አላማችንን እውን የምናደርግበትን መንገድ እንድናፈላልግ አንባቢውን ሁሉ አደራ እላለሁ።

በበኩሌ ይህ ሃሳብ ተግባረዊ ይሆን ዘንድ ለ ቤን ዌብሳይት የመሳሰሉትና ሌላ ቅን አሳቢ ኢትዮጵያውያን ጥሪየን አቀርባለሁ። ከልብ ከተመኘነውና መደረግ ያለበት ጉዳይ መሆኑ ላይ ከተማመንን በቀላሉ መደረግ የሚችል ነገር ይመስለኛል። ለዚህ የሚበቃ ድርጅት በሰሜን አሜሪካ ደረጃ መመሥረት ይቻላል። ስራው በሚገባና በሚያስተማምን ደረጃ ለመካሄዱ ካገር ቤትም ሆነ ከውጭ አገር ባለ-አደራዎች (patrons) ማግኘት አዳጋች አይሆንም።

ስለዚህም በዚህ ጥያቄ ላይ ገንቢ የሆኑ አስተሳሰቦች ይንሸራሸሩ ዘንድ ጥሪዬን አቀርባለሁኝ።

ንትርኩ ይቁም። አዲሱ ሚለኒየም ጉዟችንን ባዲስ ራዕይ እንድንጀምር እድል ሰጥቶናል። አናበላሸው።

**እንዳዲስ እንጀምር!!**

*ሣሙኤል*